HOWARD UNIVERSITY HOSPITAL

# የጨጓራና አንጀት ሕክምና ክፍል
# Division of Gastroenterology

## የትልቁ አንጀት ምርመራ (Colonoscopy) ዝግጅት መመሪያዎች

### መመሪያ 1፦ የኮሎንኮስኮፒ ቀጠሮ ከተያዘ በኋላ

- የአንጀት ማጽጃ መጠጥዎን (GoLYTELY) ከታዘዘልዎ በኋላ ወዲያውኑ ከፋርማሲ ይውሰዱ።

### መመሪያ 2 ፦ የመድሃኒት አወሳሰድ መመሪያዎች

**የደም ማቅጠኛዎችን እየወሰዱ ከሆነ**

- Xarelto®፣ Eliquis®፦ ምርመራው ከመደረጉ ከ3 ቀናት በፊት ያቁሙ።
- Plavix (ፕላቪክስ)® ምርመራው ከመደረጉ ከ 5 ቀናት በፊትያቁሙ።
- Warfarin (Coumadin®)፣ ምርመራው ከመደረጉ ከ 3 ቀናት በፊት ያቁሙ።

**ኢንሱሊን እየወሰዱ ከሆኑ**

- አጭር ጊዜ የሚቆይ ኢንሱሊን፦ ይህን በፍጹም በ ምርመራው ቀን አይውሰዱ።
- ረጅም ጊዜ የሚቆይ ኢንሱሊን፦ ምርመራው ከመደረጉ በፊት ባለው ምሽት የሚወስዱትን መደበኛ መጠን ግማሹን ብቻ ይውሰዱ።

**የ GLP-1 አጎኒስት (Agonists) መድኃኒቶችን የሚወስዱ ከሆነ (ለስኳር በሽታ ወይም ለክብደት መቀነስ የሚያገለግሉ)**

- በመርፌ የሚወሰዱ (ለምሳሌ፦ ኦዜምፒክ (Ozempic)®፣ ዌጎቪ (Wegovy)®፣ ትሩሊሲቲ (Trulicity)®ዜፕባውንድ (Zepbound)®፣ ቢሳይዝ (BCise)® እና ሙንጃሮ (Mounjaro)®)፦ ምርመራው ከመደረጉ ከ 1 ሳምንት በፊት ያቁሙ።
- በአፍ የሚወሰዱ (ለምሳሌ፦ ቪክቶዛ (Victoza)®፣ ሳክሴንዳ (Saxenda)®ባዬታ (Byetta)®እና አድሊክሲን (Adlyxin)®)፦ ምርመራው ከመደረጉ ከ 24 ሰዓታት በፊት ያቁሙ።

### መመሪያ 3፦ ከኮሎንኮስኮፒዎ አንድ ቀን በፊት

- ከጠዋት ጀምሮ ንጹህ ፈሳሾችን ብቻ መጠጣት አለብዎት። ምንም አይነት ምግብ መመገብ የለብዎትም።
- የንፁህ ፈሳሾች ምሳሌዎች ውሃ፣ ንጹህ መረቅ፣ የፖም ጭማቂ፣ ሻይ፣ ቡና (ወተት አይፈቀድም) እና ቀለም የሌለው ጋቶራዴ (Gatorade) ያካትታሉ።
- ምንም የወተት ተዋጽኦ፣ ወይም አልኮሆል አይፈቀድም።

### መመሪያ 4፦ የአንጀት ዝግጅት መመሪያዎች

**ምርመራው ከመደረጉ በፊት ያለው ምሽት**

- ከምሽቱ 6 PM እስከ ምሽቱ 8 PM ባለው ጊዜ ውስጥ ግማሹን የ አንጀት ማፅጃ መጠጥ ይጠጡ።

**በምርመራው ቀን**

- ከጠዋቱ 4AM እስከ 6AM ባለው ጊዜ ውስጥ የቀረውን የ አንጀት ማፅጃ መጠጥ ይጠጡ።
- የ ሲሜቲኮን ክኒንዎን ጠዋት የ አንጀት ማፅጃ መጠጡን እንደጨረሱ በትንሽ ውሃ ይውሰዱት።
- ከመድረሻ ሰዓትዎ ቢያንስ 2 ሰዓታት በፊት ሁሉንም የአንጀት ማጽጃ መጠጥ መጨረስ አለብዎት።
- የአንጀት ዝግጅትዎን ከጨረሱ በኋላ ምንም ነገር አይጠጡ።
- ሌላ መመሪያ ካልተሰጠዎት በስተቀር፣ አስፈላጊ የሆኑ የጠዋት መድኃኒቶችን (እንደ የደም ግፊት፣ የታይሮይድ፣ የሚጥል በሽታ እና የልብ መድኃኒቶች) በጥቂት ውሃ መውሰድ ይችላሉ።
- በሂደቱ ቀን ጠዋት ላይ ምንም አይነት በአፍ የሚወሰዱ የስኳር መድኃኒቶችን አይውሰዱ።
- ምቹ ልብስ ይልበሱ እና ውድ የሆኑ ቁሳቁሶችን ይዘው አይምጡ።

### ያስታውሱ !!!

- መታወቂያዎን፣ የኢንሹራንስ ካርድዎን እና የሚወስዷቸውን መድኃኒቶች ዝርዝር ይዘው ይምጡ።
- ኃላፊነት የሚሰማው አዋቂ ሰው አብሮዎት መምጣት ያለበት ሲሆን፣ ምርመራው ከተጠናቀቀ በኋላ ወደ ቤት ሊወስድዎት ዝግጁ መሆን አለበት።

ማንኛቸውም ጥያቄዎች ወይም ስጋቶች ካሉዎት፣ እባክዎን የጨጓራና አንጀት ህክምና ክፍልን በ 202-865-1374 ከጠዋቱ 9:30 እስከ ምሽቱ 4:30 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ያግኙ። ከሥራ ሰዓት ውጭ ለሚደረግ እርዳታ፦ በ 202-865-6100 እና በሥራ ላይ ያለውን የጨጓራና አንጀት ስፔሻሊስት (GI) እንዲያገናኙዎት ይጠይቁ። እነሱም የሚያሳስብዎትን ጉዳይ ሊፈቱልዎት ይችላሉ።